**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢ.ዴኃኅ)**
ETHIOPIAN DEMOCRATIC HIBREHIZB UNITY MOVEMENT (EDHUM)
*P.O. Box 73796 * Washington D.C. 20056-3796; E-mail: edhum2000@yahoo.com*
======= ======= =======



**ሰኔ ፲፪ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ/ም**

# የኀዘን መግለጫ፤

**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢ.ዴኅአን) በወንድማችን በክቡር ዶ/ር ደስታ ዳምጠው ከዚኽ ዓለም በሞት መለየት የተሰማውን ጥልቅ ኃዘን ሲገልፅ፤ እኚህ አገር-ወዳድ ምሁር ከልብ ለሚወዷት አገራቸውና አጥብቀው ለሚያከብሩት ሕዝባቸው በነበራቸው ወሰን የሌለው ፍቅር የሁሉም ዜጎች እኩልነት የተከበረበት ፍትኃዊ ሥርዓት እውን እንዲሆን ያደረጉትን እንከን-የለሽ ትግልና ያበረከቱትን በመልካም ምሳሌነት የሚጠቀስ አስተዋፅዖ በኩራት በመዘከር ነው።**

**ዶ/ር ደስታ ዳምጠው ለአገራቸው አንድነት ቀናዒና ለሕዝባቸው ሁለንተናዊ መብቶች መከበር የማይናወጥ አቋም የነበራቸው ታላቅ አገር-ወዳድ፣ ሲበዛ ጨዋ፣ ትሁትና ሰው አክባሪ፣ ቁጡብና ቀጥተኛ፣ ርኅሩኅና ቸር ኩሩ ኢትዮጵያዊ ነበሩ።**

**በመሆኑም፣ በተለይ ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢ.ዴኃቅ) ጀምሮ አብዛኛዎቹን የሣምንት መጨረሻ ቀናት ከሚኖሩበት ከቨርጂኒያ ቢች እየተነሱ ብዙውን ጊዜ ከትግል ጓደኛቸውና ከልብ ወዳጃቸው ከፕሮፌሰር ዓለምአንተ ገብረ-ሥላሴ ጋር በመሆን ዋሽንግተን ዲሲ ድረስ በመመላለስ በሚደረጉ ድርጅታዊ ስብሰባዎችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ደከመኝ ሰለቸኝ ሣይሉ ሲሣተፉ ቆይተዋል። ውድ ባለቤታቸው ክብርት ወይዘሮ አልማዝ አበበም በዚሁ አድካሚ ምልልስ ከጎናቸው ሣይለዩ የእንግልቱ ተጋሪ እንደነበሩ ይታወቃል።**

**ዶ/ር ደስታ ዳምጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲን (ኅብረሕዝብ-ኢትዮጵያን) ከ፲፱፻፹፭ ዓ/ም ጀምረው ፓርቲው ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ኢ.ዴኅ - ኢ.ዲዩ) ጋር ታኅሣስ ፲፮ ቀን ፪ ሺህ ዓ/ም በመዋኀድ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄን (ኢ.ዴኅአን) እስከመሠረተበት ጊዜ ድረስ በተደጋጋሚ እየተመረጡ በሊቀ-መንበርነት መርተዋል፤ በንቃት፣ በታማኝነትና በብቃት አገልግለዋል። ከዚኽ የድርጅት ኃላፊነት በተጨማሪ ፓርቲው አባል በነበረበት ኢ.ዴኃቅም ሆነ በኋላም መሥራች አባል በሆነበት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢ.ዴኃኅ) ውስጥ የተሰጧቸውን ልዩ-ልዩ ተልዕኮዎች በብቃት የተወጡ አኩሪ ታጋይ ነበሩ።**

**በአገራቸው ለውጥ እንዲኖር ባደረጉት ድርጅታዊ ትግል በተለይ የሰብዓዊ-መብት መከበርንና የዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እውን መሆንን በተመለከተ**

ትኩረት ሰጥተው ሲደክሙበትና ከአገር-ወዳድ ምሁራን ጋር አበክረው ሲመክሩበት የቆየ ጉዳይ እንደነበር ይታወቃል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ እኚህ ታላቅ አገር-ወዳድ ታጋይ ምሁር አገራቸውን እንደናፈቁ የታገሉለት የሕዝብ ጥያቄ ምላሽ ሣያገኝ ከዚኽ ዓለም በሞት በመለየታቸው ኃዘናችን ከባድ ቢሆንም፤ ውድ እናታቸው ክብርት ወ/ሮ ፀሐይወርቅ ደረዮ፣ ውድ ባለቤታቸው ክብርት ወ/ሮ አልማዝ አበበ፣ እህቶቻቸውና ወንድሞቻቸው፣ ዘመድ አዝማድ፣ ወዳጆቻቸውና የትግል ጓደኞቻቸው ሁሉ ዶ/ር ደስታ ዳምጠው ከአገር-ወዳድነትና ከንፁኅ የሕዝብ ፍቅር በመነጨ ባደረጉት ወለም-ዘለም የሌለበት የትግል ታሪካቸው ምን ጊዜም ሊኮሩ ይገባል ብሎ ያምናል።

አምላክ የታጋይ ዶ/ር ደስታ ዳምጠውን እናት፣ ውድ ባለቤት፣ እህቶች፣ ወንድሞችና ቤተሰብ ይባክር፣ ከልብ የሚወዷትንና የታገሉላትን አገረ-ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይጠብቅ።

ነፍስ ይማር!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን)